# ውሸት ነገሠ!

መስቀል አደባባይ- ህዝባችን ተጠርቶ
ሕጻን ሽማግሌው ባልቴት እና አዋቂው-
ግልብጥ ብሎ ወጥቶ
የክብር እንግዶች- ከአውሮጳ ከእስያ
ከጎረቤት ሃገር- ጅቡቲ ኬንያ
የአማሪካው ቆንሲል- ሚስተርም ተገኝተው
ጳጳሱ ተጠርተው- ካህናት ቀድሰው
ቅባ-ቅዱስ ፈልቶ-በአናቱም አፍስሰው
አክሊል ተደፋለት- እምቢልታ ተነፋ
ሕዝብ ሠገደለት- ሥልጣን ክብሩ ሰፋ
ከበሮ ተመታ-ሆታውም ቀለጠ- እልልታ ተሰማ
ውሸት ንጉሥ ሆነ- ሰርቆት አልጋ ወራሽ-በአገሬ ከተማ።

እናም የእኛ ሰፈር- ትልቅ ሽማግሌ
አንቱ የተባሉት- ትናንት እና ዛሬ
በቁርባን ያገቡት- በክርስትናቸው
ይኸው በአደባባይ -ሲዋሹ ያዝናቸው።

መቸ ይኸ ብቻ- ሆነና ነገሩ
በሃሰት ተከሰው- ተሰማና ፋይሉ
ደግነት ቅንነት- እስር ቤት ገቡ አሉ።

እንግዲህ ምን ይሉ- ዘመን ተቀየረ
ውሃ ሽቅብ አይፈስ- ሲባልም ነበረ
ዘመን ተገላብጠ - ውሸት ተከበረ።

ኑሯችን ሆነና- ከደሃው ቀምተን
እውነትን ንቀነው- ውሸትን አንግሰን
ወደፊት ለመሄድ - መራመድ አቃተን።

ዳግማዊ ዳዊት
የካቲት 2002 ዓ.ም.